ማውጫ

መግቢያ 1

ምዕራፍ ስድስት ፡ ልብስ 2

ክፍል አንድ ፡ መናገር 2

ክፍል ሁለት ፡ንባብ 3

ክፍል ሶስት፡ መፃፍ 4

ምዕራፍ ሰባት፡ የምግብ አዘገጃጀት 6

ክፍል አንድ ፡ ማዳመጥ 6

ክፍል ሁለት ፡ መናገር 7

ክፍል ሶስት፡ ንባብ 7

ክፍል አራት፡ መፃፍ 9

ምዕራፍ ስምንት ፡ ንፅህና 12

ክፍል አንድ ማዳመጥ 12

ክፍል ሁለት ፡ መናገር 14

ክፍል ሶስት፡ ማንበብ 14

ክፍል አራት መፃፍ 15

ምዕራፍ ዘጠኝ ፡-መልካም ፀባይ 17

ክፍል አንድ ፡ መናገር 17

ክፍል ሁለት ማንበብ 18

ክፍል ሶስት ፡መፃፍ 20

ምዕራፍ አስር፡የዱር እንስሳት 22

ክፍል አንድ፡ መናገር 22

ክፍል ሁለት፡ ንባብ 22

ክፍል ሶስት ፡ መፃፍ 25

ከምዕራፎቹ ለተመረጡ መልመጃዎች መልስ 26

መግቢያ

ይህ የመማሪያ ሞጁል በወቅቱ በአለም አቀፍ ደረጃ በተፈጠረው የኮሮና ቫይረስ /ኮቪድ19/ ተላላፊ በሽታ ምክንያት መንግስት በሀገራችን ውስጥ የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስ ሲባል ትምህርት ቤቶች በሽታውን መቆጣጠር እስኪቻል ድረስ ዝግ እንዲሆኑ በመወሰኑ ምክንያት ተማሪዎች በመደበኛው ፕሮግራም ትምህርታቸውን መከታተል ባለመቻላቸው በቤታቸው ሆነው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ታስቦ የተዘጋጀ የአምስተኛ ክፍል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ መማሪያ ሞጁል ነው፡፡

ይህ ሞጁል በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት እንዲማሩት ከተዘጋጁት የትምህርት ይዘቶች ተውጣጥቶ ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚያስችል መልኩ በአጭሩ የተዘጋጀ ሞጁል ሲሆን ከምእራፍ ስድስት እስከ ምእራፍ አስር አምስት ምእራፎችን አጠቃሎ ይዟዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በዚህ ሙጁል የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ምዕራፍ ስድስት ፡ ልብስ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ:-

- የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች ስም ትናገራላችሁ፡፡
- ድርብ ድምፅ ያላቸውን ፊደላት ታነባላችሁ፤ ትፅፋላችሁ ፡፡
- ሁለንም ፊደላት ታነባላችሁ፤ ትፅፋላችሁ፡፡
- ቃላትና አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን ታነባላችሁ፤ ትፅፋላችሁ፡፡

ክፍል አንድ ፡ መናገር

ተማሪዎች አሁን መናገር ችሎታችሁን የምታዳብሩበት ተግባር ትሰራላችሁ ፡፡

ተግባር አንድ

የራሳችሁንና ከቤተሰባችሁ የተወሰኑ ልብሶችን በአንድ ላይ ከሰበሰባችሁ በኋላ እያነዳንዱን ልብ እያነሳችሁና እያሳያችሁ የልብሱን ምንነትና መጠን አጠገባችሁ ለምታገኙት ሰው ተናገሩ፡፡ይህን ስታደሩጉ የምትተቀሙት ቋንቋ አማርኛ መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም እየተማርን ያለነው ይህንኑ ስለሆነ፡፡

ለምሳሌ፡1. አጭር ኮት

2. ረዥም ቀሚስ

ተግባር ሁለት

የልብሶቻችሁን ቀለም እየለያችሁ በቅርብ ላለ የቤተሰብ አባል ተናገሩ፡፡

ምሰሌ፡-1. ቀይ ቀሚስ

2. ሰማያዊ ሸሚዝ

ተግባር ሶስት

በአካባቢያችሁ የሚለበሱ ልብሶች ከምን ከምን እንደሚሰሩ በቅርብ ለምታገኙት ሰው ተናገሩ።።

ለምሳሌ፡ ጋቢ - ከጥጥ ይሰራል

ተግበር አራት

የሳምንቱን ቀናት በቅደም ተከተል ተናገሩ ።።

ክፍል ሁለት ፡ንባብ

ከዚህ በታች የቀረቡት ፊደላት ድርብ ድምፅ ያላቸው/ዲቃላ ፊደላት ይባላሉ።። እነዚህ ፊደላት ካሁን በፊት አንብባችኋቸው አታውቁም ስለዚህ ፊደላቱን እንድታነቡ የሚረዳችሁ ሰው ያስፈልጋችኋል።። በመጠኑ የቅርፅ መመሳሰል ያላቸው ፊደላት አንድ ላይ እንዲሆኑ ለማድረግ ተሞክሯል ።። በሚረዳችሁ ሰው በመታገዝ ፊደላቱን ደጋግማችሁ በማንበብ ድምፃቸውንና ቅርፃቸውን ለዩ።።

ቧ	ቷ	ኋ	ጓ	ቋ	ዟ	ሯ	ጧ	ዷ
ኋ	ቿ	ኳ	ኗ	ሟ	ኟ	ፏ	ፏ	ጇ
኿			ኟ					ፘ
			ኳ					

የሚከተሉት ቃላት ከላይ ያነበባችኋቸውን ፊደላት አካተው የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ቃላቱን አንብቡ፡፡

1. ባት
2. እሷ
3. ሻሿ
4. ልጅቷ
5. ልጆቿ
6. ቅሏ
7. ድንኳን
8. ስኳር
9. ጓደኛ
10. ኗሪ
11. ሞኟ
12. አጓት
14. ኳስ
15.ጓዳ
16. አኗኗር

ክፍል ሶስት፡ መፃፍ

ተማሪዎች

ሀ. ከዚህ ቀጥሎ የመፃፍ ችሎታችሁን የምታሻሽሉባቸው ተግባራት ቀርበውላችኋል፡፡ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተግብሩ፡፡

1. በአካባቢያችሁ የሚለበሱ የልብስ አይነቶችን ፃፉ፡፡

2. በአካባቢያችሁ አልባሳት ከምን ከምን እንደሚሰሩ ፃፉ፡፡

3. ድርብ ድምፅ ያላቸውን/ዲቃላ ፊደላት ፃፉ፡፡

4. የሳምንቱን ቀናት በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

ለ. በሚከተሉት ቃላት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን ስሩ፡፡

ምሳሌ፡- ልጅቷ ----ልጅቷ ቀጭን ነች፡፡

ኳስ------ቶላ ኳስ መጫወት ይወዳል፡፡

1. ስኳር
2. ጓደኛ
3. አጓት
4. ጓዳ
5. ድንኳን

ሐ. በሚከተሉት የልብስ አይነቶች መጠሪያ ላይ መጠን ገላጭ ቃላትን ጨምሩ፡፡ ከዚያም በቅርብ ላለ ሰው በማሳየት አስተያየት ተቀበሉ፡፡

1. ቀሚስ
2. ሱሪ
3. ሸሚዝ
4. ሹራብ
5. ኮት

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ልብስ ከምን ከምን ሊሰራ ይችላል?
2. ኳስበሚለው ቃል ውስጥ የመጀመሪያው ፊደል ምን አይነት ፊደል ነው?
3. በአካባቢያችሁ የሚለበሱ ባህላዊ ልብሶች ምን ምን ናቸው?
4. የሳምንቱ ቀናት ከ ሰኞ ጀምሮ በቅደም ተከተል ዘፉ፡፡

ምዕራፍ ሰባት፡ የምግብ አዘገጃጀት

የሚጠበቁ ውጤቶች፤ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የምግብ ዓይነትን፣ አዘገጃጀትን እና አያያዝን አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- የአመጋገብ ሥርዓትን ትናገራላችሁ፡፡
- ለተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ዝግጅት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ስምና ቅርጽ ትናገራላችሁ፡፡
- ቃላትና ዓረፍተ ነገሮችን ታነባላችሁ፣ትጽፋላችሁ፡፡
- 1-50 ያሉትን ቁጥሮች ታነባላችሁ፣ በፊደል ትጽፋላችሁ፡፡

ተማሪዎች አሁን የምዕራፍ ሰባትን ትምህርት እንቀጥላለን፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በምዕራፍ ስድስት እንዳደረግነው የቋንቋ ችሎታችሁን ልታዳብሩ የምትችሉባቸው ተግባራትና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል፡፡ ታዲያ የቀረቡላችሁን ተግባራትና መልመጃዎች በትእዛዙ መሰረት ትኩረት ሰጥቶ መተግበር ከእናንተ የሚጠበቅ ነው፡፡

ክፍል አንድ ፡ ማዳመጥ

ተማሪዎች አሁን ማዳመጥ ችሎታችሁን የበለጠ የምታዳብሩበትን አንድ ተግባር አቀርብላችኋለሁ፡፡ ታዲያ ትኩረት ሰጥታችሁ አከናውኑ፡፡

ተግባር

ከቤተሰባችሁ አንጋፋ የሆነ ሰው በአካባቢው ስለ ተለመደ ባህላዊ ምግብ በመጠየቅ ከምን እንደሚዘጋጅና እንዴት እንደሚዘጋጅ ጠይቁ፡፡ የሚሰጣችሁን ምላሽ በሚገባ ካዳመጣችሁ በኋላ ለሌላ ቤተሰብ አባል ሀሳቡን ንገሩ፡፡

ክፍል ሁለት ፡ መናገር

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ባጠገባችሁ ለምታገኙት ሰው ንገሩ፡፡

1. የምንመገበውን ምግብ ከምን ከምን እናገኛለን?
2. ምግብ እንዴት ይዘጋጃል?
3. በአካባቢያችሁ የተለመዱ የምግብ አይነቶች ምን ምን ናቸው?
4. በአካባቢያችሁ ከተለመዱ የምግብ አይነቶች አንዱን በመምረጥ አዘገጃጀቱን በቅደም ተከተል በቅርባችሁ ላለ ሰው ተናገሩ፡፡
5. በአካባቢችሁ የታወቁ ባህላዊ ምግቦችንእና ከምን እንደሚዘጋጁ በቅርብ ለምታገኙት ሰው ዝርዝር አስረዱ፡፡
6. ምግብ ለማዘጋጀት የምንጠቀምባቸው እቃዎችን ስም ተናገሩ፡፡
7. በአካባቢያችሁ የሚመረቱ ምርቶች በምን በምን ይሰፈራሉ?

ክፍል ሶስት፡ ንባብ

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የተለያዩ የምግብ አይነቶችና ከምን እንደሚዘጋጁ/እንደሚገኙ እንድታነቡ አቅርቤላችኋለሁ በጥሞና አንብቡ፡፡ ከዚያም ካነበባችሁት የሚቀርብላችሁን ጥያቄ ትሰራላችሁ፡፡

ተ.ቁ	የምግቦቹ መጠሪያ	ከምን እንደሚዘጋጅ/እንደሚገኝ
1	እንጀራ	ከጤፍ፣ ከገብስ፣ ከበቆሎ፣ ከስንዴ፣ ከዳጉሳ ከመሳሰሉት
2	ዳቦ	ከገብስ፣ ከበቆሎ፣ ከስንዴና ከመሳሰሉት
3	ስጋ	ከዶሮ፣ ከከበት፣በግ፣ፍየል፣ዓሳ፣ግመል
4	ወተትና የወተት ውጤቶች	ከላም፣ ከግመል ከመሳሰሉት
5	ብርቱካን	ከብርቱካን ተክል
6	ገንፎ	ከገብስ፣ ከበቆሎ፣ ከስንዴና ከመሳሰሉት
7	ቆሎ	ከገብስ፣ ከሽንብራ ፣ከስንዴና ከመሳሰሉት
8	ሽሮ	ባቄላ፣ አተር ፣ጓያ
9	ንፍሮ	ስንዴ፣ በቆሎ፣ ባቄላ፣ አተር

ተማሪዎች የምግብ አይነቶቹን አነበባችሁ? በጣም ጥሩ አሁን ጥያቄዎቹን ለመመለስ

ሞክሩ ::

መልመጃ አንድ

ሀ. ከላይ የቀረበላችሁን የምግብ ዝርዘርና ከምን እንደሚዘጋጅ የሚጠቁም ሰንጠረዥ አንብባችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:: መልሶቹን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ:: መልሳችሁ ትክክል መሆኑና አለመሆኑን ሰርታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ምንባቡን በማየት ማረጋገጥ ትችላላችሁ::

1. እንጀራ ከምን ከምን ሊዘጋጅ ይችላል?
2. ገንፎ ከምን ይሰራል ?
3. ሽሮ ከምን ይሰራል ?
4. ቆሎን ለማዘጋጀት ምን ምን የእህል አይነቶችን መጠቀም አለብን?
5. ወተትና ከየት ይገኛል::

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. ከላይ ካነበባችኋቸው የምግብ አይነቶች መጠሪያቸው ከሁለት ፊደላት የተመሰረቱት የትኞቹ ናቸው ?

2. ከላይ ካነበባችኋቸው የምግብ አይነቶች መጠሪያቸው ከሶስት ፊደል የተመሰረቱት የትኞቹ ናቸው?

3. ከላይ ካነበባችኋቸው የምግብ አይነቶች መጠሪያቸው አራትና ከዛ በላይ በሆኑ ፊደላት የተመሰረቱት የትኞቹ ናቸው?

ሐ. ከላይ ካነበባችኋቸው የምግብ አይነቶች ከተመሳሳይ የእህል አይነቶች ሊዘጋጁ የሚችሉትን ለያታችሁ ፉዛ፡፡

1.---------- 3.----------

2.---------- 4.----------

ክፍል አራት፡ መፃፍ

መልመጃ አንድ

ሀ. ከሚከተሉት የምግብ አይነቶች ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ ባህላዊ ምግብ የሆኑትን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

1. ጨጨብሳ
2. ጥህሎ
3. ገንፎ
4. ጭኮ
5. ጩምቦ
6. ቅንጪ
7. አምባሻ
8. አምቾ

ለ. በአካባቢያችሁ ከሚታወቁ ባህላዊ ምግቦች አንዱን በመምረጥ እንዴት እንደሚዘጋጁ በቅደም ተከተል ፃፉና ለቤተሰባችሁአባላት አቅርቡና አስተያየት ተቀበሉ፡፡

መልመጃ ሁለት

ሀ. ተማሪዎች የተለያዩ የምግብ አይነቶች ለማዘጋጀት የሚከናወኑ ተግባራትን በምሳሌው መሰረት ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡ ቆሎ ይቆላል ካልን እንጆራ ይጋገራል እንላለን፡፡

1. ለወተት ይፈላል ካልን ለጎመን ምን እንላለን
2. ለሸንኩርት ይከተፋል ካልን ለዳቦ ምን እንላለን
3. ካሮት ይፋቃል ካልን ለድንች ምን እንላለን
4. ዳቦ ይደፋል ካልን ለእንጀራ ምን እንላለን
5. ለጠላ ይጠመቃል ካልን ለአረቄ ምን እንላለን

ለ. የሚከተሉትን የምግብ አይነቶች በየትኛው የዘር ክፍል እንደሚመደቡ ከተሰጡት አማራጮች መርጣችሁ መልሱ

1. ሎሚ ሀ. ከእህል ለ. ከጥራጥሬ ሐ. ከፍራፍሬ

2. በቆሎ ሀ. ከእህል ለ. ከፍራፍሬ ሐ. ከአትክልት

3. ጤፍ ሀ. ከጥራጥሬ ለ. ከአትክልት ሐ. ከእህል

4. ጎመን ሀ. ከፍራፍሬ ለ. ከአትክልት ሐ. ከእህል

5. አንሮቴ ሀ. ከእህል ለ. ከፍራፍሬ ሐ. ከአትክልት

መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ፃፉ

ምሳሌ፡ 1------አንድ 2------ሁለት

3-----ሶስት 10-------አስር

15-----አስራ አምስት

ቁጥር	በፊደል	ቁጥር	በፊደል
12		34	
17		36	
19		38	
20		40	
22		42	
25		46	
30		48	
33		50	

ክለሳ ጥያቄዎች

1. **ምግብ ከምን ከምን እናገኛለን ?**

2. **በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ የምግብ አይነቶች ምን ምን ናቸው?**

3. **በአካባቢያችሁ የሚታወቁ ባህላዊ ምግቦች ምን ምን ናቸው?**

4. **ምግብ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ እቃዎች ምን ምን ናቸው?**

5. **በአካባቢያችሁ ለምርት መስፈሪያ የሚያገለግሉ መስፈሪያዎች ምን ምን ናቸው?**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ:-

- ስለ ንጽህና የሚቀርብላችሁን አጭር ምንባብ አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቡን ትናገራላችሁ፡፡
- የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ ለምን እንደሚያስፈልግ ትናገራላችሁ፡፡
- ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ ዓረፍተ ነገሮችንና ቁጥሮችን ታነባላችሁ፤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን በቃላት ላይ ትጨምራላችሁ፡፡
- የነገሮችን መንስዔና ውጤት ትጽፋላችሁ፡፡
- ቁጥሮችን ከ 51-100 በፊደል ትጽፋላችሁ፡፡

ተማሪዎች የምዕራፍ ስድስትና ሰባት ትምህርታችንን አጠናቀን አሁን ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ ስምንት ትምህርታችን እናልፋለን፡፡ ያለፉትን ምዕራፎች በሚገባ እንዳጠናችሁና ተግባራቱንና መልመጃዎቹን በተሰጣችሁ መመሪያ መሰረት እንዳከናወናችሁ ሙሉ እምነት አለኝ፡፡ በምዕራፍ ስምንትም የቀረቡላችሁን የትምህርት ይዘቶች እንዲሁ ትኩረት ሰጥታችሁ በመስራት በዚህ የክፍል ደረጃ ማዳበር የሚገባችሁን የቋንቋ ክህሎት እንድታዳብሩ ጠንክሮ መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡

ክፍል አንድ ማዳመጥ

ታማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ምንባብ ሌላ ሰው እንዲያነብላችሁ በማድረግ እናንተ በጥሞና አዳምጡ ከዚያም ካዳመጣችሁት ምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ሞክሩ፡፡

የማዳመጥ ምንባብ

የነ መገርሳ አካባቢ ኗሪዎች በወር ሁለት ግዜ ሁሉም ኗሪች ወጥተው አካባቢያቸው ያፀዳሉ፡፡ ኗሪዎቹ ለስራ የሚያስፈልጉ እንደ አካፋ ዶማ ማጭድ መጥረጊያና የመሳሰሉትን በመያዝ ጠዋት 12፡00 ሰዓት ላይ የመንደሩ ሽማግሌዎች የተጣላ የሚያስታርቁበት፣ ስለ መንደራቸው ጉዳይ የሚመካከሩበትና የእድር ስበሰባ በሚያደርጉበት በመንደሩ መሀል በሚገኘው የዋርካ ዛፍ ስር ይገኛሉ፡፡

ይህንን ስራ የሚያስተባብረው የቀበሌው ጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያ የሆነው ወጣት ባይሳ አበራ ነው፡፡ የጤና ባለሞያው የመጡትን ሰዎች በአራት ቡድን ከከፈለ በኋላ በመንደሩ በአራት አቅጣጫ እንዲሰማሩ ያደርጋል፡፡ በቡድን የተከፈሉት ሰዎች በተመደቡበት ቦታ በመሄድ አላስፈላጊ ተክሎችን በመንቀል፣ የተደፈኑ የውሀ መውረጃ ቦዮችን በመክፈትና በየ መኖሪያ ቤቶች በር ላይ በተለያዩ ቆሻሻ ማስቀመጫ የተጠራቀሙትን ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ በማቃጠል አካባቢያቸውን በሚገባ ያፀዳሉ፡፡

የነ መገርሳ መንደር ሰዎች የአካባቢያቸውን ንፅህና ስለሚጠብቁ መንደራቸው ሁልግዜ ንፁህ ከመሆኑም በላይ ከንፅህና ጉድለት ሊመጡ በሚችሉ በሽታዎች አይጠቁም፡፡

ተማሪዎች አሁን ያዳመጣችሁትን ምንባብ ሀሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ራሳችሁን የምትገመግሙበት ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል፡፤ ጥያቄዎቹን ለመስራት ምንባቡን መመልከት አስፈላጊ አይደለም፡፡ ጥያቄዎቹን ሰርታችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ ምን ያህል እንደመለሳችሁ ማመሳከር ትችላላችሁ፡፡

መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. የነ መገርሳ መንደር ሰዎች በወር ሁለት ግዜ የሚገኙት ለምንድን ነው?

2. በነ መገርሳ መንደር የሚከናወነውን የአካባቢን የማፅዳት ስራ የሚያስተባብረው ማነው?

3. የነ መገርሳ መንደር ሰዎች በበሽታ የማይጠቁት በምን ምክንያት ነው?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሳት በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. የነ መገርሳ መንደር ሰዎች የሚሰባሰቡት በቀበሌ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው፡፡

2. ለስራ የወጡትን ሰዎች የሚያሰማራው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያ ነው፡፡

3. የመንደሩ ሰዎች የአካባቢያቸውን ንፅህና ስለሚጠብቁ መንደራቸው ሁሌ ንፁህ ነው፡፡

ክፍል ሁለት ፡ መናገር

1. የግል ንፅናን መጠበቅ ለምን ይጠቅማል?
2. የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ ምን ጥቅም አለው?

ተማሪዎች መልሳችሁን በቅርባችሁ ላለ ሰው ተናገሩ ታድያ ስትናገሩ በአማርኛ ቋንቋ መሆን ይኖርበታል ። ምክንያቱም ይህንን ተግባር የምንሰራው በአማርኛ ቋንቋ መናገር ችሎታችንን ለማሻሻል ነው።

ክፍል ሶስት፡ ማንበብ

ተማሪዎች አሁን የማንበብ ችሎታችንን የምናዳብርበት ንፅህና በሚል ርዕስ አጭር ምንባብ አቅርቤላችኋለሁ።።ይንን አጭር ምንባብ ትኮረት ሰታችሁ ለማንበብ ሞክሩ።።ምንባቡን አንድ ጊዜ ወየም ሁለት ጊዜ አንብቡና ያበባችሁትን ምንባብ ሀሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ራሳችሁን የምትገመግሙበት ጥያቄዎችን አቅርቤላችኋለሁ።። ጠያቄዎቹን ስትሰሩ ምንባቡን መመልከት አይፈቀድም።። ጥያቄዎቹን ሰርታችሁ ስትጨርሱ ምን ያህል እንደመለሳችሁ ለማመሳከር ምንባቡን ማየት ትችላላችሁ።።

ንፅህና

ንፅህና ስንል የግልና የአካባቢ ንፅህናን ያጠቃልላል። የግል ንፅህና ስንል የሰውነታችንንና የልብሳችንን ንፅህና ያጠቃልላል ። የሰውነታችን ንፅህና ማለትም የእጃችንን፣ የፊታችንን ፣ የአፋችንና የጥርሳችንን እንዲሁም የፀጉራችንን ንፅህና ሲያካትት ፤ የልብሳችን ንፅህና የቀንና የሌሊት ልብሳችንን ያጠቃልላል። የአካባቢ ንፅህና ደግሞ የቤታችንና የመኖሪያ አካባቢያችንን የሚያጠቃልል ነው። የሰው ልጅ በጤንነት ለመኖር የግሉንና የአካባቢውን ንፅህና መጠበቅ ይኖርበታል። የግልና የአካባቢ ንፅህና መጓደል በጤናችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ችግር ሊፈጥርብን ይችላል። ስለዚህ ዘወትር የግልና የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ ይገባል።

መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ

1. ንፅህና ምን ምንን ያጠቃልላል?
2. በግል ንፅህና ስር የሚካተቱት ምን ምን ናቸው?
3. የግልና የአካባቢ ንፅህና መጓደል ምን ሊያስከትል ይችላል?

4. የሰው ልጅ በጤንነት ለመኖር ምን ማድረግ አለበት?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ

1. የግል ንፅህናን መጠበቅ ስንል መላ አካላችንን ማለታችን ነው።
2. የግልና የአካባቢን ንፅህና በመጠበቅ ጤንነታችንን መጠበቅ እንችላለን።
3. የግል ንፅህናችንን ለመጠበቅ ልብሳችንን ማጠብ ብቻ በቂ ነው።
4. ቀን የምንለብሰው ልብስ ንፁህ ከሆነ የሌሊት ልብሳችን ንፁህ ባይሆንም ችግር የለውም።

ክፍል አራት መፃፍ

ሀ.የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ከግዜ አመልካች ቅጥያዎች ጋር ተጣምረው የቀረቡ ናቸው እናንተ ሀላፊ ግዜ፣ ያሁን ግዜ እና የወደፊት ግዜ በማለት ለይታችሁ ፃፉ

ምሳሌ፡- ይመጣል--- ወደፊት ግዜን ያመለክታል።

1. መጥቷል
2. እየሄደ ነው
3. ሰርቷል
4. ይሰራል
5. እየሰራ ነው

ለ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች በመንስኤና በውጤት ተጣምረው የቀረቡ ናቸው እናንተ መንስሌውንና ውጤቱን ለይታችሁ ፃፉ

ምሳሌ፡ ንፅህናን ያለመጠበቅ ለበሽታ ያጋልጣል።

መንስኤ፡ ንፅህናን ያለመጠበቅ

ዉጤት፡ ለበሽታ ያጋልጣል

1. ሴና ንፅህናዋን ስለምትጠበቅ ሁሌ ደስተኛ ነች።

2. የነ ገረሱ መንደር ሰዎች የአካባቢያቸውን ንፅህና ስላልጠበቁ ለተላላፊ በሽታ ተጋለጡ።

3. መረርቱ ንፅህናው ያልተጠበቀ ውሃ ጠጥታ ታመመች፡፡

4 የልብሳችንን ንፅህና ከልጠበቅን መጥፎ ጠረን ይኖረናል፡፡

5. ፊይሳ እጁን ሳይታጠብ ተመግቦ ለሆድ ህመም ተጋለጠ፡፡

ሐ. ስለ ንፅህና ጥቅም ከቤተሰብ አባላቶቻችሁ ውስጥ አንድ ሰው ጠይቁና ያገኛችትን ሀሳብ ፃፉ፡፡ ጠይቃችሁ የተረዳችሁትን ደግሞ ለሌሎች የቤተሰብ አባለት አስረዱ፡፡

መ. የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

ምሳሉ፡ 60----- ስልሳ 75-----ሰባ አምስት 89-----ሰማንያ ዘጠኝ

ቁጥር	በፊደል	ቁጥር	በፊደል
52		88	
56		90	
64		91	
68		93	
78		99	
87		100	

የክለሳ ጥያቄዎች

1. የግልና የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ ለምን ይጠቅማል?

2. መገርሳ የቤት ስራውን ሰርቷል፡፡ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሰርቷል የሚለለው ቃል የሚያመለክተውን ግዜ ተናገሩ፡፡

3. የግል ንፅህና ምን ምንን ያጠቃልላል?

ምዕራፍ ዘጠኝ ፡-መልካም ፀባይ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የመልካም ባህሪ መገለጫዎች ምን ምን እንደሆኑ ትናገራላችሁ፡፡
- መመሪያዎችን ከመደብ አንፃር ትናገራላችሁ ፡፡
- ቃላትን በማጥበቅበት በማላለት ታነባላችሁ፤ትፅፋላችሁ፡፡
- ከቃል ሌሎች ቃላትን ትመሰርታላችሁ፡፡
- የተዘበራረቁ አረፍተ ነገሮችን አስተካክላችሁ ትፅፋላችሁ፡፡

ተማሪዎች አሁን በምዕራፍ ዘጠኝ ስር የተካተተቱ የትምህርት ይዘቶችን ማጥናት እንጀምራለን፡፡እ ንደተለመደው ትህርታችሁን በትኩረት ለመከታተል ራሳችሁን ማዘጋጀት ይኖርባችኋል፡፡ ውድ ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ ልታውቋቸው የሚባችሁንእውቀቶችና የቋንቋ ክሂሎች ለማሻሻል የናንተ የግል ጥረት በጣም አስፈላጊ መሆኑን አሁንም ደግሜ ላሳስባችሁ እወዳለሁ፡፡

ክፍል አንድ ፡ መናገር

ተማሪዎች አሁን የመናገር ችሎታችሁን የበለጠ የምታዳብሩበት ተግበር አቅርቤላችኋለሁ ታዲያ ተግባራቱን በታለማችነት ተግብሩ፡፡ በኣማርኛ ቋንቋ የመናገር ችሎታችሁን ለማዳበር ተግባራቱን ስትሰሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋችሁን መጠቀም የለባችሁም፡፡

ተግባር1

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ መልሳችሁን ለቤተሳባችሁ አባለትተናገሩ፡፡ በመጨረሻም እነርሱ የሚሰጧችሁን አስተያየተ ተቀበሉ፡፡

1. መልካም ባህሪ የሚባሉት ምን አይነት ባህሪያት ናቸው?
2. መጥፎ የሚባሉ ባህሪያትስ ምን ምን ናቸው?
3. ታማኝነት የምን ባህሪ ምልክት ነው?
4. ያለመታዘዝ የምን ባህሪ ምልክት ነው?

5. መሳደብ የምን ባህሪምልክት ነው?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት በቃል መልሱ

1. በትምህርት ቤት መልካም ባህሪ ያለው ተማሪ በተማሪዎችና በመምህራን ይወደዳል።
2. የተቸገረን መርዳት ከመጥፎ ባህሪያት ይመደባል።
3. መልካም ባህሪ ያለው ሰው በመንግስትና በህዝብ ይፈለጋል።
4. መልካም ባህሪና መጥፎ ባህሪ ተቃራኒ ናቸው።
5. መጥፎ ባህሪ ያለው ሰው ለራሱም ሰላም አይኖረውም።

ክፍል ሁለት ማንበብ

የሚከተሉትን የመልካምና የመጥፎ ፀባይ መገለጫዎችን አንብቡ።

የመልካም ፀባይ መገለጫዎች	የመጥፎ ፀባይ መገለጫዎች
መረዳዳት	ያለ መታዘዝ
መከባበር	መናናቅ
ስራን ማክበር	መዋደድ
መተጋገዝ	የሰውን ሀሳብ ማንቋሸሽ
እውነት መናገር	መዋሸት
ቸርነት ማድረግ/መስጠት	መስረቅ
ሀቀኝነት	ማጭበርበር
ፍቃደኛ መሆን	እንቢተኝነት
ትሁት መሆን	ትቢተኛ መሆን
ያለማዳላት	ስራን መናቅ

መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ ባነበባችሁት ምንባብ ሀሳብ መሰረት መልሱ።

1. ቸርነት ማድረግ የምን አይነት ፀባይ መገለጫ ነው?
2. ስራን ያለማክበር ምን አይነት ፀባይን ያመለክታል?
3. ፍቃደኛ ከመሆንና ከእንቢተኝነት መልካም ፀባይን የሚያመለክተው የቱ ነው?
4. ለታላላቆቻችን መታዘዝ የትኛውን ፀባይ ያንፀባርቃል?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።

1. መሳደብ የመልካም ባህሪ መገለጫ አይደለም።
2. ታላላቆችን ማክበርና መታዘዝ የመልካም ባህሪ መገለጫ ነው።
3. መመሪያዎችንና ደንቦችን ማክበር መልካም ባህሪ አካል ነው።
4. መልካም ባህሪ ማሳየት ያለብን በትምህርት ቤት ብቻ ነው።
5. አንድ ሰው የሚሰርቅ ከሆነ ጥሩ ባህሪ እንደሌለው ማሳያ ሊሆን ይችላል፡

መልመጃ ሁለት

ሀ. በሚከተሉት ቃላት አጫጨር ዐ.ነገር ሰርታችሁ አንብቡ

1. ባህሪ
2. ማክበር
3. ታላቅ
4. ዘወትር

ክፍል ሶስት ፡መፃፍ

ውድ ተማሪዎች አንዳንድ ቃላት ጠበቀውና ላልተው ሲነበቡ የትርጉም ልዩነት ያመጣሉ፡፡
ለምሳሌ ፡ አለ የሚለው ቃል ጠብቆ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጉም 'መኖርን 'ሲያመለክት
ቃሉ ላልቶ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጉም ደግሞ 'ተናገረ' የሚል ይሆናል፡፡
መልመጃ አንድ

ሀ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በማጥበቅና በማላላት በማንበብ ሲጠብቁና ላልተው ሲነበቡ የመሰጡትን የትርጉም ልዩነት አስተውሉ፡፡

1. ገና
2. በላ
3. ዋና
4. ለጋ
5. ሳለ
6. ሞቃት
7. አያት

ለ. በሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ከስራው የተሰመረባቸውን ቃላት በማጥበቅና በማላላት አንብበችሁ ትርጉም ልዩነታቸውን በቅርብ ለምታገኙት ሰው ተናግሩ፡፡

1. ቶለሳ እቤት ውስጥ <u>አለ</u>፡፡
   ቶለሳ ወደ ትምህርት ቤት ልሄድ ነው <u>አለ</u>፡፡
2. <u>የገና</u> በአል በጣም ደስ ይለኛል፡፡
   እሸቱ <u>ገና</u> አልደረሰም፡፡
3. ገመቹ ምሰውን በላ፡፡
   መምህሩ ተማሪውን በላ አለው፡፡
4. ሀሰን በውሀ ዋና ውድድር አሸነፈ፡፡
   ብሪቱ የክፍሉ ዋና ተጠሪ ነች፡፡
5. ቃሪያው ለጋ ነው፡፡
   በረኛው ኳሱን ለጋ፡፡

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል ከአንድ ቃል ሌሎች ቃላትን መመስረት እንዴት እንደሚቻል እናያለን፡፡ ከአንድ ቃልሌሎች ቃላትን ለመመስረት የፊደላቱን ቦታ በመቀያየርና የተወሰኑ ፊደላትን በማስቀረት ለለሆን ይችላል፡፡የምንመሰርታቸው ቃላት ተርጉም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ምሳሌ፡ ይኖራቸዋል ፡፡ ኖራ፣ ይዋል፣ ዋል፣ቸል፣ይኖራል

ሐ. ቀጥሎ ከተሰጡት ቃላት ሌሎች ቃላትን መስርቱ

1. እንክብካቤ
2. የሚያነቡላችሁን
3. በማስቀረት
4. በተጨማሪም
5. ቃላት

መ. በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉት ተዘበራረቁ ቃላት በቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ ለምሳሌ፡- ገበያ መገርቱ ሄደች፡፡ መገርቱገበያ ሄደች፡፡

1. የቤት ስራ ተፈራ ሰራ፡፡
2. ነው ጥሩ መታጠብ እጅን፡፡
3. በላ ምሳውን ከበደ፡፡
4. አልወድም ተማሪ ሰነፍ እኔ፡፡
5. ትናንት ገዛ መኪና መገርሳ፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1. የመልካም ባህሪ መገለጫዎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው
2. የመጥፎ ባህሪ መገለጫዎች ምን ምን ናቸው
3. ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የትርጉማ ልዩነት የሚያስከትሉ አምስት ቃላትን ፃፉ

የሚጠበቁ ውጤቶች፡

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ:-

- የዱር እንስሳት መጠሪያዎችን ትናገራላችሁ።
- የዱር እንስሳትን ጥቅም ትናገራላችሁ።
- ለዱር እንስሳት ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤ ትናገራላችሁ።
- በቃላት ዐ.ነገር ትፅፋላችሁ።

ክፍል አንድ፡ መናገር

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የመናገር ችሎታችሁን የምታዳብሩበትን ተግባር ቀርቦላችኋል። ተግባራቱን በሚገባ ትኩረት ሰታችሁ መስራት ይኖርባችኋል። ይህን ተግባር ስታከናውኑ መጠቀም ያለባችሁ አማርኛ ቋንቋን ነው።

ተግበር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከነበባችሁ በኋላ መልሳችሁን በቅርብ ለምታገኙት ሰው መናገር ትችላላችሁ።

1. በአካባቢያችሁ ምን ምን አይነት የዱር እንስሰት ይገኛሉ?
2. የዱር እንስሳት ከቤት እንስሳት በምን ይለያሉ?
3. የዱር እንስሳት በሰው ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ተናገሩ።
4. የዱር እንስሳት ለሰው ልጅ ምን ጠቀሜታ ይኖራቸዋል?

ክፍል ሁለት፡ ንባብ

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የዱር እንስሳት በሚል ርእስ ምንባብ ቀርቢላችኋል። ምንባቡን ለማንበብ ምቹ የሆነ ቦታ በመምረጥ አንድጊዜ ወይም ሁለት ገዜ አንበብቡ። ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች በመመለስ የምንባቡን ሀሳብ ምን ያክል እነደተረዳችሁ ራሳችሁን ገምግሙ።

የዱር እንስሳት

የዱር እንስሳት የሚኖሩት በደን ውስጥ ነው። ምግባቸውንም የሚያገኙት ከሚኖሩበት ደን ውስጥ ነው ። የዱር እንስሳት እንደ ቤት እንስሳት ሁሉ ለሰው ልጆች ጠቀሜታ አላቸው። ለምግብነት ፣ለቱሪስት መስህብ በመሆንና የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ለሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክረታሉ።

የዱር እንስሰት ለሰው ልጅ የሚሰጡት ጥእምና ለሀገር እድገት የሚያበረክቱት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲቀጥል ከተፈለገ እንስሳቱን ልንከባበባቸውና ልንጠብቃቸው ይገባል። የዱር እንስሳቱን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ደግሞ የእንስሳቱ መኖሪያ የሆነውን ደን በእንክብካቤ መያዝና በየግዜው ከሚደርስበት ህገወጥ ጭፍጨፋ መጠበቅ ሲሆን በተጨማሪም ያለአግባብ እየተካሄደ ያለውን ህገ ወጥ አደን መከላከል ነው። አለበለዚያ ግን እንስሰቱ ሌላ መኖሪያ ፍለጋ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ጎረቤት ሀገሮች ይሰደዳሉ። ይህ ደግሞ ሀገሪቱ ከዱር እንስሳት ልታገኝ የሚገባትን ጠቀሜታ ስለሚያሳጣ በሀገሪቱ እድገት ላይ ተፅእኖው ከፍተኛ ይሆናል።

የዱር እንስሳት ጠቀሜታ እንዳላቸው ሁሉ ጉዳትም አላቸው። አንዳንድ እንስሳት በቤት እንስሳትንና በሰውን ልጅ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላለ። ለምሳሌ፡-ጅብ የቤት እንሰሳትን እንደ አህያ ፈረስ በቅሎና መሳሰሉት በመብላት የሰውን ልጅ ችግር ላይ ይጥላል።

መልመጃ አንድ

ባነበባችሁት ምንባብ ሀሳብ ላይ ተመርኩዛችሁ የሚከተሉት ጥያቄዎች መልሱ።

1. ከቤት እንስሳትና ከዱር እንስሳት ለሰው ልጅ የበለጠ ጠቀሜታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

2. የዱር እንስሳት መኖሪያ በእንክብካቤ ካልተያዘ በእንስሳቱ ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ ምን ሊሆን ይችላል?
3. ከዱር እንስሳት ውስጥ በሰው ልጅ ላይ ጉዳት ከሚያስከትሉ እንስሳቶች ውስጥ አምስቱን ስም ፃፉ ::
4. የዱር እንስሳትን ባሉበት ሁኔታ ለመንከባከብ ምን ማድረግ ይኖርብናል?
5. ሰዎች እንስሳትን ለምን ያድናሉ?

መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የዱር እንስሳት ስም ካነበባችሁ በኋላ ለሰው ልጅ የሚሰጡትን ጠቀሜታና የሚያደርሱትን ጉዳት ለይታችሁ ፃፉና በቅርብ ለምታገኙዋቸው ሰዎች አንብቡላቸው::

ለምሳሌ--ጅብ -----ጠቀሜታው የሞቱ እንስሳትን በማንሳት በአካባቢው መጥፎ ሽታ እንዳይኖር ያደርጋል::

ጉዳቱ:- የቤት እንስሳት በመብላት::

1. ዝሆን
2. አንበሳ
3. ቀበሮ
4. ከርከሮ
5. ሚዳቋ
6. ጅብ

መልመጃ አንድ

በሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ዐ.ነገር ስሩ።

ምሳሌ፡- መኖሪያ -- ደን የእንስሳት መኖሪያ ነው።

1. ጠቀሜታ
2. የውጭ ምንዛሪ
3. እንክብካቤ
4. ቀዳሚ ተግባር
5. ህገ ወጥ
6. መጨፍጨፍ

መልመጃ ሁለት

የቤት እንስሰትና የዱር እንስሳት ለሰው ልጅ ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር አወዳድሩና ሀሳባችሁን በፅሁፍ አስፍሩ ከዚያም ለቤተሰባችሁ አባላት አቀርቡና የሚሰጧችሁን አስተያየት ተቀበሉ።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. የዱር እንስሳትና የቤትእንስሳት ልዩነታቸው ምንድን ነው?
2. የዱር እንስሳት በሰው ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ጉዳት ምን ሊሆን ይችላል?
3. የዱር እንስሳት ለሰው ልጅ በምን መንገድ ይጠቅማሉ?

ከምዕራፎቹ ለተመረጡ መልመጃዎች መልስ

ምዕራፍ ስድስት

ክፍል ሶስት

ሀ. 1. የተለያዩ መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ።።

2. ከጥጥ፣ ከቆዳ ፣ከሱፍ

3. ሁሉንም ድርብ ድምፅ ያላቸውን ፊደላት

4. ሰኞ፣ ምክሰኞ ፣እሮብ ፣ሀሙስ፣ አርብ ፣ቅዳሜ፣ እሁድ

ለ. የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ

ሐ. 1. አጥር ቀሚስ ረዥም ቀሚስ

2. ሰፊ ሱሪ ፣ አጭር ሱሪ፣ ረዥም ሱሪ ፣ጠባብ ሱሪ

3. ወፍራም ሹራብ ስስ ሹራብ

4. ረዥም ኮት፣ አጭር ኮት

ምዕራፍ ሰባት

ክፍል ሁለት መልመጃ አንድ

ሀ. ከጠፍ፣ ከስንዴ ፣ከገብስ

ለ. ከገብስ፣ ከበቆሎ፣ ከስንዴ ፣አጃ

ሐ. ባቄላ ፣አተር ፣ጓያ ፣ሽንብራ

መ. ሽንብራ ገብስ ስንዴ

ሠ. ከላም ከግመል

ለ. 1. ጤፍ፣ ዳቦ ፣ስጋ ፣ ቆሎ ፣ ሽሮ

2. ቀተት ፣ ገንፎ ፣ ንፍሮ

3. እንጅራ፣ ብርቱካን

ሐ. 1. እንጀራ ፣ዳቦ ፣ገንፎ

2. ሽሮና ንፍሮ

3. ስጋና ወተት

ክፍል አራት

መልመጃ አንድ

ሀ. ጨጨብሰ ፣ ገንፎ ፣ ጭኮ ፣ ጨንቦ ፣ ቅንጬ

መልመጃ ሁለት

ሀ. 1. ይቆላል

2. ይቆረሳል

3. ይላጣል

4. ይጋገራል

5. ይወጣል

ለ. 1. ሐ

2. ሀ

3.ሐ

4.ለ

5. ሐ

ምዕራፍ ስምንት

ክፍል አንድ

ሀ. 1. አካባቢያቸውን ለማፅዳት

2. የጤና ኤክቴንሽን ባለሞያ

3. አካባቢያችን ስለሚያፀዱ

ለ. 1. ሀሰት

2. እውነት

3. እውነት

ክፍል ሶስት

መልመጃ አንድ

ሀ. 1. የግልና የአካባቢ ንፅህና

2. የሰውነትና የልብስ ንፅህና

3. በጤናችን ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል

4. የግልና የአካባቢንፅህና መጠበቅ

ለ.1. እውነት

2. እውነት

3. ሀሰት

4. ሀሰት

ክፍል አራት

ሀ. 1. ሀላፊ ጊዜ

2. የአሁን ጊዜ

3. ሀላፊ ጊዜ

4. የወደፊት ጊዜ

5.የአሁን ጊዜ

ለ. 1. መንስኤ፡ ሴና ንጽህናዋን ስለጠበቀች

ውጤት፡ ሁሌ ደስተኛ ነች

2. መንስኤ፡ የአካባቢያቸውን ንፅህና ስላልጠበቁ

ውጤት ፡ለተላላፊ በሽታ

3. መንስኤ፡ ንፅህናው ያልተጠበቀ ውሀ ስለጠጣች

ውጤት፡ ታመመች

4.መንስኤ፡ የልብሳችንን ንፅህና ካልጠበቅን

ውጤት፡ መጥፎ ጠረን ይኖረናል

5.መንስኤ፡ እጃን ሳይታጠብ ተመግቦ

ውጤት፡ ለሆድ ህመም ተጋለጠ

ምዕራፍ ዘጠኝ

ክፍል አንድ

ተግባር አንድ

1. ትህትና፣ መታዘዝ፣ ስራን ማክበርና የመሳሰሉት

2. ስርቆት ፣ስራን መናቅ ፣ መሳደብና የመሳሰሉት

3. መልካም

4.የመጥፎ

5. የመጥፎ

ለ. 1. እውነት

2. ሀሰት

3. እውነት

4. እውነት

5.እውነት

ክፍል ሁለት

ሀ. 1. የመልካም

2. **መጥፎ**

3.**ፈወቃደኛ መሆን**

4. **መልካም ባህሪ**

ለ. 1 እውነት

2. **እውነት**

3.**እውነት**

4. **ሀሰት**

5. **እውነት**

መልመጃ ሁለት

ሀ. የተለያዩ መልሶች ሊሰጡ ይችላሉ።።

ክፍል ሶስት

ሀ	**ቃል**	**ላልቶ ሲነበብ**	**ጠብቀው ሲነበቡ**
1.	**ገና**	**አልደረሰም**	**የክርሰቶስ ልደት በአል**
2.	**በላ**	**ተናራ**	**ተመገበ**
3.	**ዋና**	**መዋኘት**	**ሀላፊ/ተጠሪ**
4.	**ለጋ**	**ያልበሰለ**	**መታ/ለኳስ**

5. ሳለ	ለስዕል/ለስለት /በጉንፋን	የኖረ ግዜ
6. ሞቃት	ሙቀት ተሰማት	ሞቃት አየር
7. አያት	የእናት/የአባት/እናትና አባት	ተመለከታት

ሐ. 1. ክብ፣ እንካ

2. ቡላ ፣ ሁን፣ ችላ ፣ የሚያነቡ

3. ማሰ፣ በቀረ ፣ ቀረ፣ በረት፣ ማበስ

4. ጨማሪ ፣ ማሪ ፣ ተጨማሪ

5. ላት

መ. 1. ተፈራ የቤት ስራ ሰራ።።

2. እጅን መታጠብ ጥሩ ነው ።።

3. ከበደ ምሳውን በላ።።

4. እኔ ሰነፍ ተማሪ አልወድም።።

5. መገርሳ ትናንት መኪና ገዛ።።

ምዕራፍ አስር

ክፍል ሁለት

መልመጃ አንድ

1. የቤት እንስሳት

2. ወደ ሌላ ቦታ መሰደድ

3.አንበሳ፣ ነብር ፣ጅብ ፣ቀበሮ ፣ተኩላ

4. ደኖችን መጠበቅ

5. ለምግብነት፣ ቆዳቸውን ፣ጥርሳቸውን ፣ቀንዳቸውን በመሸጥ ገንዘብ ለማግኘት።